# የመዘምራን አገልግሎት

በወይዘሮ ውሂብ ዘውዴ

ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን
መዘምራን የተሰጠ ስልጠና

# የመዘምራን አገልግሎት

በወይዘሮ ውሂብ ዘውዴ

ስለ መዘምራን አገልሎት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር ከተፈለገ አስቀድሞ አገልግሎት ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## I. አገልግሎት ምንድን ነው?

የእግዚአብሔርን ቃል ስንመረምር ስለ አገልግሎት ምንነት የተሰጡትን መሠረታዊ ሃሳቦች እናገኛለን። እነዚህንም መሠረታዊ ሃሳቦች መረዳት አገልግሎታችን የበለጠ ትርጉም እንዲሰጠንና ለአገልግሎታችንም ከፍተኛ አክብሮት እንዲኖረን ይረዳናል። ከብዙ በጥቂቱ አገልግሎት ምን እንደሆነ በሚከተሉት ነጥቦች ማየት እንችላለን፦

1. አገልግሎት የደህንነታችን አንዱ ዓላማ ነው

እግዚአብሔር በፀጋው ብቻ አድኖናል። ከኃጢአትና ከሰይጣን ባርነት ነጻ አውጥቶን ትርጉም ያለው ኑሮ እንድንኖር አድርጎናል። ነገር ግን የዳንነው በደስታ ለመኖር ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም እንድናገለግለው ጭምር ነው።

«በእርሱም ከጠላቶቻችን ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን።» ሉቃስ 1፥74-75

«ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ!» ዘፀአት 8፥1

የጴጥሮስ መልዕክት ላይም የዳንንበትን ዓላማ ሲናገር «እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝቦች ናችሁ።»ይላል። 1ኛ ጴጥሮስ 2፥9

2. አገልግሎት የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ነው

እግዚአብሔርን ሳይወዱ ማገልገል ይቻላል (ለሥራ፣ለመተዳደሪያ፣ለገንዘብ፣ ለዝናና ለመሳሰለው።) ነገር ግን እግዚአብሔርን እየወደዱ እግዚአብሔርን አለማገልገል አይቻልም። የጌታ ፍቅር የነካው ሰው የግድ ሌሎችን ከፍቅር የተነሣ ያገለግላል።

ዮሐንስ 21፥15-19 ባለው ክፍል ስናነብ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ትወደኛለህን? ብሎ ይጠይቀውና በልን እንማር፤ መቀባበል ለቡድን ሥራ እጅግ ጠቃሚ ነው። ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼን፣ በጎቼን መግብ - ጠብቅ በማለት ሌሎችን እንዲያገለግል ይጠይቀዋል።

ስለዚህ ጴጥሮስ ክርስቶስን ያገለግል የነበረው ክርስቶስን ከመውደድና ከማፍቀር የተነሳ እንደሆነ እንረዳለን። ዛሬም ጌታ የሚወዱትን ሁሉ አገልግሎት ላይ በመሰማራት ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር እንዲገልጹ ይፈልጋል።

3. አገልግሎት ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ሃላፊነት/ሹመት ነው

ማቴዎስ 24፥51 ላይ ጌታ በምሳሌ ሲያስተምር፦ «ጌታው በቤተሰቦቹ ላይ የሾመው ...» ሲል እኛ አገልጋዮቹ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ **ኃላፊነት** የተሰጠን፣ **የተሾምን** መሆናችንን ይጠቁማል። ጌታ በሌሎች ላይ እንድንሰለጥንባቸው ሳይሆን **ዝቅ** ብለን እንድናገለግላቸው ይጠብቅብናል።

4. አገልግሎት መንፈሳዊ አደራ ነው

2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥6 ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ «መልካሙን አደራ ጠብቅ።» በማለት የተሰጠው አገልግሎት የወንጌል አገልግሎት አደራ እንደሆነ ያስገነዝበዋል። እንዲሁም ዛሬ እኛ የምንሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ከጌታ የተቀበልነው አደራ መሆኑን አውቀን ማገልገል አለብን። **እግዚአብሔር በእኛ ታምኖ የአገልግሎትን አደራ ከሰጠን** እኛም በእርሱ ታምነን አደራውን ልንጠብቅ ይገባናል።

5. አገልግሎት የሚያስጠይቅ ኃላፊነት ነው

እግዚአብሔርን ማገልገል ደስታንና በረከትን ያስገኛል፤ ነገር ግን ደግሞ እንዴት እንደሰራን፣ፍሬ አፍርተንና አላፈራን እንደሆነ በራሱ በእግዚአብሔር እንጠየቃለን። ማቴዎስ 25፥14-30 ላይ ከጌታ መክሊት (የአገልግሎት ስጦታ) የተቀበሉትን የተለያዩ ሰዎች በመጨረሻው ስለተቀበሉት ኃላፊነት እንደተጠየቁ እንመለከታለን። ኃላፊነታቸውን የፈጸሙትን «ታማኝ ባሪያ» በማለት ለበለጠ ሹመት ሲያጫቸውና ወደ ጌታቸው ደስታ እንዲገቡ ሲፈቅድላቸው እናያለን። የተቀበለውን መክሊት በመቅበር ኃላፊነቱን በመዘንጋት ፍሬ አልባ የሆነው ሰው ግን «ሃኬተኛ ባሪያ» በመባል ተፈረደበት። የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው። ማቴዎስ 25፥19 ዛሬስ ጌታ እኛን ቢቆጣጠረን ሃላፊነታችንን እንዴ ት ባለ ሁኔታ እየተወጣን ነው?

## II. የመዝሙር አገልግሎት

የመዝሙር አገልግሎት የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያንን ለማሳደግ የሚቀርበውን የእግዚአብሔርን ቃል የሚረዳ፣ የሚያጠናክርም አገልግሎት ነው። በእግዚአብሔር የተቀቡ ዘማሪያን የሚዘምሩበትን ስብሰባ መካፈል እጅግ የሚባርክ ነው።

1. አዲስ ኪዳን በግልጽ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ዝማሬዎች እንዳሉ ይናገራል። ኤፌሶን 5፥18-19 «በመንፈስ ተሞሉ በመዝሙርና፣ በዝማሬ፣ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ ። ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ።» በማለት አንዱ በመንፈስ የመሞላት ምልክት ለጌታ መዘመርና

መቀኘት እንደሆነ ያሳየናል። እንደገናም ቆላስይስ 3፥16 ላይ «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ . .. በመዝሙርና በመንፈሳዊም ቅኔ በፀጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።»ይላል።

2. ብሉይ ኪዳን ውስጥ 1ኛ ዜና መዋእል 25 ላይ የትንቢት አገልግሎትንና የሙዚቃን/የዝማሬን አገልግሎት ያያይዝልናል።

ይህ ክፍል ሙዚቃና ትንቢት ያላቸውን መጣመር ያመለክታል። .በሙዚቃው መካከል ተነበዩ ወይም በሙዚቃ ተነበዩ።» ማለት ይቻላል። 1ኛ ሳሙኤል 10፥5-6 ሳሙኤል ለሳኦል ሲነግረው፥ «ወደ ከተማይቱ እንደደረስክም የነቢያት ጉባኤ በመሰንቆ፣በከበሮ፣በእምቢልታና በበገና ታጅበው ታገኛቸዋለህ።»
2ኛ ነገሥት 3፥14-15 ላይም ኤልሳዕ ለመተንበይ የሙዚቃን አገልግሎት ሲጠይቅ እናያለን።

3. ሙዚቃ/ዝማሬ የሰዎችን ልብ ስለሚያለሰልስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማትና ለመቀበል እንዲችሉ መንገድ ይፈጥራል፤ ሰዎችን ያዘጋጃል።

ሳኦል በክፉ መንፈስ ተይዞ በነበረበት ጊዜ ዳዊት በገና ሲደረድርለት ነፃነት ያገኝ ነበር።

4. ሙዚቃ/ዝማሬ ጥንትም በብሉይ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ነበረው።

«በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ምስጋናና ውዳሴ እንዲያቀርቡ በመሰንቆ በበገና ይዘምሩ ነበር።» 1ኛ ዜና 16፥4-8 [1ኛ ዜና 25፥1-31, 2ኛ ዜና 5፥12-14] ይነበብ

በአጠቃላይ የመዝሙር አገልግሎት በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈና ትክክለኛ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባ አገልግሎት ነው። የመዘምራን አገልግሎት ለአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙ ሰዎች (ከልምምድ እንዳየነው) በመዝሙር አገልግሎት በክርስቶስ የሚገኘውን ደህንነት አግኝተዋል።

## III. መዘምራን አምላኪዎች ናቸው

በአምልኮ ውስጥ ጸሎት (ልመና) እና ምስጋና አብረው ስለሚደረጉ ብዙ ጊዜ በእነዚህ ሦስት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለው ልዩነት ጎልቶ አይታይም። ነገር ግን፦

1. ጸሎት (Prayer)
2. ምስጋና (Praise)
3. አምልኮ (Worship) የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ፦

«ጌታ ሆይ አድነኝ» ብንል መጸለያችን ነው። «ስለአዳንከኝ አመሰግንሃለሁ» ብንል ማመስገናችን ነው።« ታላቅ አዳኝ ስለሆንክ አመሰግንሃለሁ» ብንል ደግሞ ማምለካችን ነው።

በአጠቃላይ አምልኮ ስንል በውስጡ ጸሎትና ምስጋና ቢኖርበትም፤እግዚአብሔርን ስለእግዚአብሔርነቱ

ብቻ ስናመሰግነውና ከፍ ከፍ ስናደርገው ነው። እግዚአብሔርን ስለሥራው፣ ስለችሎታው፣ ስለአምላክነቱ ስናከብረው ማምለካችን ነው። ማስተዋል ያለብን፥ እግዚአብሔርን ማምለክ ለአማኞች በእግዚአብሔር የተሰጠ ታላቅ ችሮታ መሆኑን ነው። ፍጥረት ሁሉ ያመሰግነዋል። መዝ.148፥1-10 እንደሚለው የባህር ዓሳና ጉንዳን ሳይቀር ያመሰግኑታል። ሆኖም እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታትን እንዲያመልኩት ሲጠይቅና ሲፈልግ አናይም። ሰውን ግን ፈለገ። እንድናመልከው ምርጫንና ዕድልን ሰጠን።

ስናመልክ የሚከተሉትን ሃሣቦች እናስታውስ፦

1. ዮሐንስ 4፥23 «አብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱለትን ይፈልጋል።» ይላል።

በዚህ ጥቅስ መሠረት አብ ራሱ እንድናመልከው ጥሪ ሲያደርግልን እናያለን፤ በተጨማሪም በዚህ ጥቅስ እውነተኛ አምልኮ፥

ሀ. በመንፈስ (በውስጠኛው ሰው) *'Inner man'* ለ. በእውነት *(right information)* ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት እናያለን ስለዚህ እውነተኛ አምልኮ ስሜትንና አእምሮን ይጠይቃል ማለት ነው። ጌታን ስናመልክ፦ የእግዚአብሔርን ማንነት አውቀንና ተረድተን፣ (እውነትን) እንዲሁም ከስሜት (ከልባችን)፥ ከውስጥ መንፈሳችን መሆን አለበት።

2. አምልኮ እንደ ሥራና እንደ ግዴታ መደረግ አይገባውም።

አምልኮ በደስታና በፍቅር መሆን አለበት። እውነት ላይ ተመርኩዘን ከስሜታችንና ከልባችን ጌታን በመንፈሳችን መገናኘት አለብን። ለማምለክ ፈቃደኞች እንደሆንን ለመግለጽና እግዚአብሔርን «ላመልክህ እወዳለሁ።» ልንለው ይገባል። «በፍጹም ልቤ፣ በፍጹም ሃሣቤ፣ በፍጹም ነፍሴ ላምልክህ ጌታዬ።» ልንለው ይገባል።

3. አምልኮ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የሁልጊዜ ነው።

መዝሙረኛው ዳዊት እንዳለው መዝሙር 134፥1 «እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፣ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው።» በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንገኝ እግዚአብሔርን ማምለክ ይገባናል።

4. እግዚአብሔርን ማየት ከፈለግን እናምልከው።

በአንድ የአምልኮ ስብሰባ ላይ ጥያቄው እግዚአብሔር ነበረ ወይስ አልነበረም አይደለም። ጥያቄው መሆን ያለበት «እግዚአብሔርን በእርግጥ አምልከህ/አምልከሽ ነበረ ወይ?» ነው። ይህንን ሃሣብ ዘጸአት 24፥1-11 ላይ እናያለን እግዚአብሔር ራሱ እነሙሴን ለአምልኮ ሲጠራቸው/ ሲጋብዛቸው እናያለን። ከዚያም ፥

ሀ.. ሕጉን በማንበብ

ለ. በአንድ ድምጽ

ሐ. በአንድ ልብ - ሲያመልኩ ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔርን እንዳዩ እናነባለን። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማየት ከፈለግን ከልብ እናምልከው።

5. እግዚአብሔር እንደገናም በባሪያው በዳዊት በኩል ሕዝቡ እንዲያመልኩት ጥሪ ያደርጋል።

በመዝሙር 95፥1-7 መሠረት እግዚአብሔርን በሚከተሉት መንገዶች ማምለክ ይቻላል።
ሀ. በሆታና በዝማሬ፥ የእግዚአብሔርን እውነት በዜማ እየተናገርን፣ ድምጻችንን ከፍ በማድረግ፣ እልል እያልን፣ ሆ! እያልን፣ ታላቅነቱን እንድናውጅ ጌታ ይወዳል። ሆ! እያልን ስናደንቀው፣ «እግዚአብሔር የሚሠራውን ማን ሊሠራው ይችላል?» ማለታችን ነው። ማድነቃችን ነው።

አንድን የስፖርት ክለብ በመደገፍ ስታድየም ገብተን በችሎታውና በአሸናፊነቱ ተደንቀን በጩኸታችን ናበሆታችን ስታዲየሙን የምንነቀንቅ ከሆነ ታላቁ አምላካችን ለሠራው አስደናቂ ሥራ የምናመልክበትን ቦታ በሆታችን መነቅነቅ አይበዛበትም ስሜታችንን ለማርካት ሳይሆን - ለጌታ ክብር።

ለ. በውዝዋዜ ማምለክ ይቻላል። ማርያም በከበሮ፣ዳዊት በሽብሸባ አምልከዋል።

ሐ .በስግደትም ጌታን ማምለክ ይቻላል። በመዝሙር 95፥6-7 እንደተገለጸው አምልኮ መንበርከክን፣ መስገድን ይጨምራል።

መ. ሌላው የአምልኮ መንገድ ዝምታ/ጸጥታ ነው። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ስናስብ ቃላት ያጥረናል ዝም እንላለን። ዘካርያስ 2፥13 «*እግዚአብሔር ከተቀደሰ ማደሪያው ተነስቷልና ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቱ ጸጥ ይበል*» ይላል።

6. መዘምራን እግዚአብሔርን በመዝሙራችን ስናመልክ የአምልኮ አድማጭ (*Audience*) እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ማስታወስ አለብን። አምልኮ ለእግዚአብሔር ነው። ሊጠየቅ የሚገባው እኛ (ዘማሪዎች) ጥሩ ስሜት ተሰማን ወይ? ሳይሆን፣እግዚአብሔር በአምልኮአችን ምን ተሰማው? ነው። የምንሰበሰበው እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው። የእኛን ስሜት ለማርካት አይደለም።

ወደ እግዚአብሔር ቤት **ለመስጠት** ነው የምንመጣው። በዝማሬያችን፣ በአምልኮአችን ተደስቶ እግዚአብሔር ካጨበጨበልን ያን ጊዜ ግባችን ተፈጽሟል። የምንወደው መዝሙር ሲዘመር ደስ ደስ እንዲለን የማንወደው ሲሆን ደግሞ ሊደብረን አይደለም። የምንዘምረው ለኛ ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ነው። በመዝሙር መርካትና *'enjoy'*ማምለክ ይለያያል። የምንዘምረው የኛን ስሜት ለማርካት ሳይሆን ለጌታ መሆኑን አንርሳ።

## IV. መዘምራን ሊኖራቸው ስለሚገባው ባሕሪያት

1. መዘምራን ከላይ እንደጠቀስነው ራሳቸው **አምላኪዎች** መሆን አለባቸው። የሚዘምረውን የማያው ቅ ወይም የሚዘምረው መዝሙር ምንም ትርጉም ለራሱ የማይሰጠው ሰው ሌላውን ሰው ወደ
2. እግዚአብሔር በዝማሬ ሊያቀርብ አይችልም።

2. መዘምራን ጥሩ የመንፈሳዊ ሕይወት፣ ለእግዚአብሔር አክብሮትና ፍቅር ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። ቤተክርስቲያን የሚያስፈልጓት «ተዋንያን» ሳይሆኑ የተለወጡ የእግዚአብሔር ሰዎች/አገልጋዮች/መሆን ይጠበቅባቸዋል።

3. ዘማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ጥሩ ምስክርነት እንዲኖራቸው ይገባል። ጠብ አነሳሺ፣ተሳዳቢ፣ የቅድስና ሕይወት የሌላቸው ከሆኑ በአንድ እጅ የገነቡትን በሌላው እጅ የሚያፈርሱ ይሆናሉ።

4. መዘምራን ከሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያን ዓላማና ራእይ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው። ከቤተ ክርስቲያኒቱ እረኛ፣ ሽማግሌዎችና አስተማሪዎች ጋር በሕብረትና በስምምነት ማገልገል የሚችሉ መሆን አለባቸው። ለሚገለገሉባትና ለሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያን **ታማኝ** መሆን አለባቸው። ዘጸአት 32፥26

5. መዘምራን የእግዚአብሔር ቤት ፍቅር ሊኖራቸው ይገባል፥ ዳዊት በቤትህ መጣል ይሻለኛል ይላል። ሌዋውያኑም ከመቅደሱ አጠገብ አይጠፉም ነበር። ከማንም ይልቅ እግራቸው ወደ እግዚአብሔር ቤት መፍጠን ያለበት መዘምራን መሆን አለባቸው። በሚደረጉትም የጸሎት የአምልኮና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁሉ መገኘትና የእግዚአብሔርን ቤት ማድመቅ በአገልግሎቶቹም መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

6. የትህትና መንፈስና የአገልጋይ ልብ ሊኖራቸው ይገባል።

7. የተቀደሰ/የተለየ ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል።

ዘኁልቁ 8፥5-11 በሚያነጻ ውኃ (በእግዚአብሔር ቃል) በየዕለቱ መታጠብ፤ ባህርይን በእግዚአብሔር ቃል ማረቅ፣ ሌዋውያን ገላቸውን ይላጩ እንደ ነበር መዘምራንም መጥፎ ባሕርይን በጌታ ጸጋ ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ሌዋውያን ልብሳቸውን ያጥቡ እንደ ነበር የመዘምራንም '*attitude*'s መንጻትና መስተካከል አለበት። በአዕምሮ መታደስ መለወጥና በጸሎት መትጋትም ተቀዳሚ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል።

8. በተጨማሪም ዘማሪያን መስዋዕታዊ የሆነ መሰጠት ለአገልግሎታቸው ያስፈልጋቸዋል። በሚያገለግሉብ ት ቤተክርስቲያን ውስጥ ፕሮግራምና አገልግሎት ሲኖር በሌላ ስፍራ ካለ ስብሰባ ይልቅ ለኅብረታቸውና ለአገልግሎታቸው መስጠት ይገባቸዋል።

9. የመዘምራን አገልግሎት የመድረክ አገልግሎት ስለሆነ የዳኑ ምዕመናንም ሆኑ የሌሎች እንግዶች

ዓይን በመዘምራኑ ላይ ማረፉ አይካድም። ስለዚህ በዕለታዊ አረማመዳቸው ዘማሪያን አገልግሎታቸው እንዳይነቀፍ የእግዚአብሔርንም ስም ለማስከበር ጥንቃቄን በማድረግ ለሌሎች ጥሩ ምሳሌነት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

10. ዳዊት እግዚአብሔርን ለማምለክ **ከፍተኛ ዋጋን ከፈለ**። 2ኛ ሳሙ.ኤል 24፥18-25። ዘማሪያንም ዛሬ የዚያኑ ያህል ዋጋ ይጠበቅብናል።

## V. የመዘምራን አገልግሎት የቡድን አገልግሎት ነው

ቡድን (*team*) ማለት፥ የተወሰኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው በሕብረትና በስምምነት በተሰጣቸው ስጦታ በመጠቀም የሚያገለግሉበት ስብስብ ነው። የመዘምራንም አገልግሎት እንዲሁ ነው ። በጌታ የዳኑ ሰዎች በሕብረትና ስምምነት የድምጽ ችሎታቸውንና የሙዚቃ ችሎታቸውን በማዋሃድ ዝማሬን በማቅረብ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበት ስብስብ ነው።

የቡድንን ሥራ ሊገልጹልን የሚችሉ ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም አንዱ የእግር ኳስ ጨዋታ ነው። ኳስ ተጫዋቾቹ ማሰብ ያለባቸው እንዴት የራሳቸውን (የግል) ችሎታቸውን እንደሚያሳዩ ሳይሆን እንዴ ት እርስ በርስ እንደሚቀባበሉና ኳሲቷን ወደ አንድ አቅጣጫ (ግብ) እንደሚመቱ ነው።

በቡድን አገልግሎት ውስጥ፦ የቡድን መንፈስ፣ የቡድን ግብና የቡድን ጨዋታ አለ።

1. **የቡድን መንፈስ** (*Team-spirit)* ፡ሲኖር ብቻ ነው የቡድን ተጫዋች (*Team-Player*) መሆን የሚቻለው ።

2. **የቡድን ግብ**፥ ግባችን የየግል ሳይሆን የሕብረቱ (የቡድኑ) ግብ መሆን አለበት። የቡድኑ ግብ መሳካት ከግለሰቦች ግብ መሳካት ይልቅ ተቀዳሚ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል። ለግል ስኬት ሰዎች በሚደክሙበት ሥፍራ ሁል ጊዜ የቡድን ዓላማ ይበደላል።

3. **የቡድን ጨዋታ**፥ አንዳችን ከአንዳችን ጋር እንዴት እንደምንተባበር ኳስን እንዴት እንደምንቀባበል (የሃሣብ ልውውጥ) እንዴት እንደምናደርግ ማሰብ ለቡድኑ ሥራ አስፈላጊ ነው። የቡድን ሥራ የመስማማትን መመሪያ የተከተለ ነው።

ከላይ እንደጠቀስነው የመዘምራን አገልግሎት የቡድን (የሕብረት) አገልግሎት ስለሆነ፤ መዘምራን የሕብረት አገልግሎት ምንና እንዴት መሆኑን ማወቁ ይጠቅመናል።

በሕብረት ማገልገል ብዙ ጥቅምን ያስገኛል። ከብዙ በጥቂቱ፥

1. **ብዙ ውጤት ያስገኛል**፦ ዘዳግም .32፥30, ምሳሌ11፥14, ምሳሌ15፥22, ምሳ.ሌ 24፥6, መክብብ 4፥9 -13፤ እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ ከተናጠል ይልቅ በብዛት (በሕብረት) መሥራት የተሻለ ውጤት የሚያመጣ

መሆኑን ያሳየናል።

2. **እርስ በርስ መሳሳል ይቻላል፡-** ምሳሌ 27፥17 «ብረት ብረትን ይስላል»።አብረን በምንሰራበት ጊዜ አንዳችን ከአንዳችን ጥበብን፣ አሰራርን፣ ሌሎችንም ብዙ ነገሮችን እንማራለን።

3. **እርስ በእርስ መጠባበቅ** (Protection)አለበት። አንዳችን ስንደክም ሌሎቻችን እንረዳለን፤ ማንም ለብቻው ሁሉን ማድረግ አይችልም። በችግር ጊዜ እርስ በእርስ እንረዳዳለን። አፈጣጠራችን ራሱ ከተናጠል ይልቅ ሕብረትን የሚጠይቅ ነው። አንዱ ያላየውን ሌላው ማየት ይችላል። ዓይኖቻችን እንኳን
ያሉት ፊት ለፊት ያለውን ለማየት ብቻ ነው። ከኋላችን ለማየት የግድ የሌሎች ዓይን ያስፈልገናል።

4. **ብርታትና ኃይል ይሰጣል፡-** በቡድን በትብብር ስንሠራ ብዙ ብርታትና ጥንካሬ እናገኛለን። አባቶቻችን «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!» ይላሉ፤ መክብብ 4፥9-12 «አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ይላል።» በሦስት የተገመደም ገመድ ጥንካሬውን መገመት እንችላለን። በተለይ ዘዳግም 32፥30 ላይ ስምምነትና ትብብር ያለውን ከፍተኛ ኃይል አጉልቶ ያሳያል። አንድ ሰው 1,000 ሲያባርር ሁለት ሰዎች ማባረር የሚችሉት 10,000 እንደሆነ ያሳየናል።

እንግዲህ ከላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች እንዳየነው ልዩ ልዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችም በአንድነት ለእግዚአብሔር ክብር ሲውሉ የሚያፈልቁት የዜማ ቃና ነፍስንና መንፈስን የሚያድስ ነው። ልዩ ልዩ ሴቶችና ወንዶችም በአንድነት ተሰባስበው ድምጻቸውን በማዋሃድ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ውዳሴና ዝማሬ ወደር የማይገኝለት አገልግሎት ነው።

## VI. መዘምራን ሊገጥሟቸው የሚችሉ መሰናክሎችና መፍትሔዎቻቸው


ምንም ዓይነት አገልግሎት መሰናክል አለው፤ ችግሮቹን አስቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ስለሆነ ጥቂቶቹን እንዘረዝራለን

1. **የተሰጠንን ኃላፊነት አለማወቅ፡-** በምንም አገልግሎት ውስጥ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎችና ልዩ ልዩ የሹመት ቦታዎች አሉ። በመዘምራን ጓድም ውስጥ ስናገለግል የተለያዩ የሥራ ዘርፍ ሊኖረን ይችላል ለምሳሌ፥ ሙዚቃ ተጫዋቾች፣ Social -eventsአዘጋጆች፣ የመዝሙር መጻሕፍት ሰብሳቢና አዘጋጅ፣ የመዘምራን ጓድ መሪዎች የገንዘብ ያዥና የመሳሰሉ። ስለዚህ ኃላፊነታችን እስከምን ድረስ መሆኑን አውቀን በተሰጠን ኃላፊነት መሥራት ውጤታማ ያደርገናል።


2. **የመሪዎችን ሥልጣን አለመቀበል፡-** አንዳንድ ሰዎች ሁል ጊዜ መሪ እንጂ በሌሎች ሰዎች መመራትን አይወዱም። ስለዚህም የሌሎችን ሥልጣን መቀበል ያቅታቸዋል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሥርዓትንና መሪዎችን አድርጓል፤ ሆኖም የቤተክርስቲያን መሪዎች በዓለም ካሉት መሪዎች የተለዩ ናቸው።

በዓለም ያለው መሪ በትሪያንግሉ ጫፍ ላይ ሲሆን ሌሎቹ ሁሉ ያሉት ከታች ነው።

(የዓለም መሪ)



ጌታ በአዲስ ኪዳን እንዳስተማረው ደግሞ ክርስቲያን መሪ ያለው ከትሪያንግሉ በታች ነው። ትሪያንግሉ ራሱ ከላይ ወደታች የተገለበጠ ነው። ሌሎቹ ያሉት ከላይ ሲሆን መሪው ከታች ነው።



(የክርስቲያን መሪ)

በክርስትና ውስጥ ያለው ሹመት «ሎሌያዊ መሪነት» ነው። (Servant Leadership)

ዮሐንስ 13፥14-16

ማቴዎስ 20፥27-28

ክርስቲያን መሪዎች (የመዘምራን መሪዎች) በትህትና መምራት ሲገባቸው፣ የመዘምራንም አባላት መሪዎችን ተገቢ ቦታቸውን መስጠትና አመራራቸውን መቀበል ያስፈልጋቸዋል፤ ልንጸልይላቸውና ልናበረታታቸው ይገባል።

3. **የውድድር መንፈስ፦** ማወቅ ያለብን፣ በጌታ ቤት ውድድር የለም። ጌታም ልጆቹን አያወዳድርም። እኛ የሥራ ባልደረባዎች ነን እንጂ ባላንጣዎች አይደለንም። 1ኛ ቆሮንቶስ 4፥1-2 ላይ ጳውሎስ ራሡንና ሌሎችን፦

1. መጋቢዎች ነን (ባለአደራዎች)
2. ሎሌዎች ነን ይላል።

4. **ግልጽ ያለመሆን፦** የግልጽነት ጉድለት የቡድንን ሥራ ይጎዳል። ረቂቅነትና ሚስጥራዊነት ቡድኑ በነጻነት የሐሳብ ልውውጥ እንዳያደርግ ያደርጋል። የመዘምራንን አገልግሎት በተመለከተ ነገር ሁሉ በግልጽ መነጋገር አስፈላጊ ነው።

5. **የሐሳብ ልውውጥ አለማድረግ፦** ግምት ብዙ ጊዜ ሰዎችን ከችግር ላይ ይጥላል። በግምት ሁሉን ነገር ማወቅ አይቻልም። ችግርም ሆነ አወያይ ጉዳይ ካለ በግልጽ ተወያይቶ መፍታት ይገባል። ድብብቆሽ መጫወትና አትድረሱብኝ ማለት ሲበዛ የሃሣብ ልውውጥ ማድረግ ይቆማል። ይህ እንዳይሆን ሥርዓትን በተመለከተ መንገድ የሃሣብ ልውውጥ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

6. **በሌላው ቦታ ራሥን አለማስቀመጥ፦** «በሌላው ጫማ ሳትቆም በፊት አትፍረድ።» የሚሉት እውነተኛ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ቃልም በማቴዎስ 7፥1 ላይ «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ።» ይላል። ብዙ ጊዜ ነገርን እኛ ካለንበት ሁኔታ ብቻ ስንመለከት የሰዎች ሃሣብ አይገባንም፣ የሌሎችን አመለካከት አንረዳም። በሌላው ዐይን ነገርን ለማየት ብዙ ትዕግሥትና ልበ ሰፊነትን ይጠይቃል።

7. **ለአገልግሎት አለመስጠት፦** መሠጠት የጎደለው ነገር ሁሉ የትም አይደርስም። ያለመሰጠት የሚሠሩ ነገሮችም መልካም ውጤት አያመጡም። መሰጠት በሌለበት፥ ትዳር አያብብም፣ ልጆችም ተቃንተው አያድጉም፣ ሥራም ስኬት አያገኝም።

በአገልግሎት አካባቢ ትልቁ ችግር ሰዎች ለአገልግሎታቸው አለመሰጠታቸው ነው። ሰይጣን የሚጠላው ነገር ቢኖር ለእግዚአብሔር ሥራ መሰጠታችንን ነው። ራስን አለመስጠት ማለት ራስን አለማስገኘት /አለማቅረብ፣'available'አለመሆን ማለት ነው።

**መሰጠት**(Commitment) ከተበታተነ አቅጣጫ አእምሮአችንን ወደ ማዕከሉ ማለትም ወደ ዋናው ዓላማ ችን ያመጣናል። እግዚአብሔር ከወርቅ ወይም ከብር የተሰራ ዕቃ አይፈልግም። እግዚአብሔር የሚፈልገው የተሰጠን ሰው ነው። ከተሰጠንለት፥ ምንም ጉድለት ቢኖረን ያንን አሟልቶና ሸፍኖ ሊጠቀምብን ይችላል።

8. **አለመቀባበል፦** እርስ በእርስ አለመቀባበል ለሕብረት አገልግሎት ትልቅ እንቅፋት ነው። ስለዚህ እር ስ በእርስ መቀባበል የግድ አስፈላጊ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በሕይወታቸው እንዲያድጉ ብቻ ሳይሆን በቡድን እንዲሠሩ አሰለጠናቸው። ነገሩ ቀላል አልነበረም። አስራ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ነበሩ። በመካከላቸውም የልምምድ፣ የሙያ፣ የትምህረት፣ የአስተዳደግ፣ የቤተሰብ፣ የእድሜና የመሳሰሉት ልዩነቶች ነበሩአቸው።

ይህ ሁሉ መቀባበል ባይኖር ችግር ሊያመጣ ይችል ነበር። ጌታ ባዘጋጀው ቡድን ውስጥ **በቂ የአገልጋዮች በሽታ ነበር**። ነገር ግን ጌታ ያስተማራቸው እንዲቀባለሉ ነበር። እነርሱም ስለተቀባበሉ ወንጌልን በአንድነት አሰፋፉ።

ልዩነቶቻችንን ለመልካም ብንጠቀምበት ይረዳናል። በጥንት ክርስቲያኖች ውስጥ ልዩነቱ ብዙ ነበር፤ ሥራውን ግን አልጎዳም። ምክንያቱም እርስ በርስ የተቀባበሉ ነበሩ። ጌታ እኛን እንደተቀበለን መቀባበል።

9. **የትዕቢት መንፈስ፦** በሰዎች ምስጋናና ሙገሣ ምክንያት የትዕቢት መንፈስ ሊፈጠር ይችላል። ትዕቢ ት ደግሞ ሰውን ይጥላል። ትዕቢት 'Sub-Conscious' ውስጥ መሰወር የሚችል ስለሆነ ያለብን ላይመስ ለን ይችላል፤ ስለዚህ ራሳችንን በመመርመር መራመድ አለብን።

10. **ቸልተኝነት፦** «*የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ ርጉም ይሁን።*» ይላል ኤርምያስ 48፥10. አገልጋይ ሁሉ ስንፍናንና ተስፋ በመቁረጥ የሚመጣውን ቸልተኝነት መዋጋት ይገባዋል።

11. ***ራስ ወዳድነት፦***የመዘምራን አገልግሎት የሕብረት አገልግሎት ስለሆነ የራሳችንን 'Interest' ወደጎን መተው አለብን። የተለያየ 'Mood' ይኖሩናል፤ በተለያየ የሕይወት ደረጃ ላይ እንገኝ ይሆናል ሆኖም «እኔ ብቻ ያልኩት ይሁን!» ከማለት ይልቅ የመዘምራኑን ዓላማ ማስቀደም ይገባል።

12. ***ትዕግሥት ማጣት፦*** ሁሉም ሰው መዝሙር እኩል ላይገባው ይችላል፤ በዚህን ጊዜ ትዕግሥት ከማ ጣት ይልቅ እርስ በርስ በመደጋገፍ ማጥናትና ሁሉም አባል መዝሙሩን እስኪያጠና ድረስ በትዕግሥት መጠባበቅ ያስፈልጋል።

13. ***መታረምን አለመውደድ፦*** ጠቢብ ሰው ከስህተቱ ይማራል። እርስ በርስ ካልተራረምን ስህተታችንን ካላወቅን የተስተካከለ አገልግሎት መስጠት ስለማንችል ዕርማትን እንቀበል።

14. **የመንፈስን አንድነት አለመጠበቅ፦** በመዘምራን መካከል ፍጹም የሆነ አንድነት ያስፈልጋል። በአን ድ ልብና መንፈስ ስናገለግል እግዚአብሔር በመካከላችን ይሠራል፥ በመዝሙር 133፥1 ላይ እንደምናነ በው በረከትና ሕብረት የማይለያዩ ነገሮች ናቸው። የአንድነትን መንፈስ የሚያጠፉ ነገሮች እንዳይፈጠ ሩ እያንዳንዱ የመዘምራን አባል መትጋት አለበት። ኤፌሶን 4፥3

## VII አጠቃላይ መመሪያ

1. እያንዳንዱ ዘማሪ በመዘምራን የአምልኮና የጸሎት ጊዜ መገኘት አለበት። ለጥናት ብቻ ሳይሆን ከ መዝሙር ጥናት በፊት በሚደረገው የጸሎት ጊዜ ላይ በመገኘት መንፈሱን ከሌሎች ጋር አንድ ማድረ ግ ይገባል።

2. የስብሰባ (የጥናት) ሰዓትን ማክበር። የአንድ ሰው ማርፈድ የመዘምራን አባላትን ሁሉ ጊዜ እንደሚጎ ዳና እንደሚያባክን ማሰብና በሰዓት መገኘት።
25 አባላት ቢኖሩና አንድ ሰው 5 ደቂቃ ቢያረፍድ የሚያባክነው 25X5=125 ደቂቃዎችን ነው።
3. ለመዘምራን አገልግሎት ዕድገትና ጥንካሬ የሚጠበቅብንን ሁሉ ማድረግ፣ ተሳታፊ መሆን፣ በተለይም ደግሞ በግል ጸሎታችን አገልግሎቱን መደገፍ።

4. ጎን ለጎን ተቀምጠን ለረዥም ሰዓት ስለምናጠና አጠገባችን ያለው ሰው እንዳይቸገርብን ንጽሕናችንን መጠበቅ (ገላን መታጠብ፣ ጥርስን መቦረሽ፣ ዲዎድራንት መጠቀምና መሳሰሉት።)

5. በመሪዎች የሚሰጠንን ማንኛውንም አይነት ዲሲፕሊን በትህትናና በቀና መንፈስ መቀበል።

6. በመዘምራን መተዳደሪያ ደንብ የወጣውን መመሪያና ሕግ  መከተልና መፈጸም።

7. እግዚአብሔር ቤት ውስጥ በጥንቃቄ እንደ ባለ አእምሮ መመላለስ። «ያለ ልባብና ያለልጓም መገታት እንደማይችሉት አእምሮ እንደሌላቸው ፈረሶችና    በቅሎዎች አትሁኑ።» መዝሙር 32፥9

8. በአገልግሎታችን 'Excellence' እናሳይ፣ በሚገባ እናገልግል፣ ለእግዚአብሔር ትራፊያችንን ሳይሆን ዋናውን ነገራችንን እንስጥ። ሚልክያስ 1፥6-10

*«እንግዲህ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የምስጋና መስዋዕት ዘወትር ለእግዚአብሔር እናቅርብ»* **ዕብራውያን** 13፥15

**እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ጸጋውን ያብዛልን!!**